የ ሰ/ማቁ. 231196

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ **መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም.**
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ዳኞች፡-

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘውዲቱ አስቻለው

ተጠሪ፡- አቶ ዮሴፍ እውቀቱ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው። በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 04 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 90793 በግንቦት 19 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን የሰጠው ፍርድ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 271867 በግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በመሻሩ እና ይኸው በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 229564 በሰኔ 25 ቀን 2014 ዓ.ም በማጽናቱ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው።

ጉዳዩ የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሆኖ መልስ በጽሁፍ የማቅረብ መብት መታለፍን የሚመለከት ነው። ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች አመልካች፣ተጠሪ ደግሞ ተጠሪ ነበሩ።

የክርክሩ መነሻ አመልካች የፍቺ ውሳኔ ካሰጡ በኃላ የንብረት ክፍፍል አቤቱታ አቅርበው ለተጠሪ የፍ/ቤቱ መጥሪያ ደርሶት ተጠሪው መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ቀነ ቀጠሮ መልስ ባለማቅረቡ የስር ፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያለበቂ ምክንያት መልሱን አላቀረበም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሚል የተጠሪውን መልስ የማቅረብ መብት አልፎ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በተጠሪ ስም በለገጣፎ የካስዬን ቀ/ገ/ማ በ300 ካ.ሜ የተገነባ ቤትና ይዞታ፣በተጠሪ ስም የተመዘገበ የሰሌዳ ቁ አ.አ 02-01-27359 የሆነ ተሸከርካሪ፤ በተጠሪ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ዳሽን ባንክ የሚገኝ ገንዘብ እንዲሁም አመልካችና ተጠሪ ከአመልካች እናት ከወ/ሮ ዓለም ወርቁ የተበደሩት ብር 60,000 የጋራ ናቸው በማለት አንዲካፈሉ ውሳኔ ሰጥታቷል፡፡

ተጠሪ ለቀረበብኝ ክስ መልስ የማቅረብ መብቱ ያለአግባብ ታልፋል በማለት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ አቅርበዋል፡፡በአቤቱታቸውም አመልካች ላቀረቡብኝ ክስ መልስ እንድሰጥ የተላከልኝ መጥሪያ ግልጽነት የጎደለው መቼ መልስ እንደማቀርብ የማይገልጽ ነው፤ የስር ፍ/ቤት በላከው መጥሪያ ላይ ቀኑ የማይነበብ ሆኖ በዕለቱ የተቀጠረበት ምክንያት ያልተገለጸ ስለመሆኑ ገልጨ ያቀረብኩ ቢሆንም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በጽሁፍ መልስ የማቅረብ መብቴን ማለፉ አግባብ ስላልሆነ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ ተጠሪ መልስ ያላቀረብኩት ችሎት ተሳስቼ፣ ረፍዶብኝ እና መጥሪያው ግልጽ አይደለም በማለት የተለያየ ምክንያት አቅርቧል፡፡ መጥሪያው መልሱ መቼ እና የት እንደሚቀርብ በግልጽ ተቀምጦ ነው የተላከለት በመሆኑ ተጠሪ መልሱን ያላቀረበው በቸልተኝነት ነው፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ቃለ መሀላም የለም ስለዚህ በጽሁፍ መልስ የማቅረብ መብቱ መታለፉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ እና የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀን 25/03/2013 ዓ.ም ለተጠሪ የተላከው መጥሪያ ዋናው ቅጂ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ ፍ/ቤቱ በቀን 26/08/2014 ዓ.ም በተላከ ምላሽ መጥሪያ ለተጠሪ በስር ፍ/ቤት በ25/3/13 ዓ.ም እንዲላክ በታዘዘው መሰረት መጥሪያ ወጪ በሚሆንበት ጊዜ የችሎት ጸሃፊ በስህተት በ25/03/13 የተጻፈውን መጥሪያ ተጠሪ በቀን 30/03/2013 ዓ.ም ፈርመው የወሰዱበትን ቀሪ በማያያዝ ልኳል፤ ከተላከው መጥሪያ መረዳት የሚቻለው መጥሪያው በተገቢው መንገድ መቼ መልስ ማቅረብ መቼ የቃል ክርክር እንደሆነ በግልጽ ይገልጻል የሚባል ቢሆን የስር ፍ/ቤት ለተጠሪ የላከው መጥሪያ መልስ ለማዘጋጀት በፍትሐብሄር ስነ-ሥርዓት ህጉ ሊሰጥ የሚገባው የአስር ቀናት ፈቃድ የጠበቀ ስላልሆነ ተጠሪ መልስ ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ ሳይሰጠው መልስ በጽሁፍ የማቅረብ መብቱ የታለፈ መሆኑን ያሳያል ፤ ስለሆነም ከስር ፍ/ቤት ለተጠሪ የተላከው መጥሪያ በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ ለመስጠት ለተጠሪ መጥሪያው ስላለመድረሱ ከስር ፍ/ቤት የቀረበው መዝገብ የሚያመላክት ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ለተጠሪ ተገቢውን መልስ የማቅረቢያ ጊዜ በመስጠት በጽሁፍ ተቀብሎ ግራቀኙን በድጋሚ ያከራክር ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልገው ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሐምሌ 04 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ በግራቀኙ ክርክር የአሁን አመልካች በተጠሪ ባቀረቡት ክፍች ጋር ተያይዞ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ታዘው ቀርበው መልስ ባለመስጠታቸው ፍ/ቤቱ የፅሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸውን ያለበቂ ምክንያት ቀርተዋል በማለት ወደ ቃል ክርክር መስማት ሲገባ ቀርበው ተከራክረው ማስረጃ ተስምቶ በዋናው ጉዳይ ውሳኔ ሲሰጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ የፅሁፍ መልስ ባለመስጠቱ ባግባቡ አልተከራከረም ስለሆነም የፅሁፍ መልስ ሳልሰጥ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ ወደ ክርክሩ ልግባ በማለት ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት ያገኘበትን አግባብ ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት እንዲሁም አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው ለተጠሪ የተላከው መጥሪያ ላይ የተገለጸው ዕለት በትክክል አለመገለጹን እና መልስ ለማቅረብ የተሰጠውም ጊዜ በሕጉ በተገለጸው አግባብ በቂ ጊዜ ሊባል የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ፍርድ ቤት ቀጠሮ በሚሰጥበት ጊዜ ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ በሚገባ እንዲከናወን አስፈላጊ መስሎ የታየውን ትእዛዝ መስጠት ያለበት በመሆኑ በቀረበ ክስ ላይ ተከሳሽ እንዲቀርብ እና የመከላከያ መልሱን እንዲያቀርብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 94 መሰረት የሚላክ መጥሪያ አባሪ ሰንጠረዥ 2 ቁጥር 1 በተመለከተው መሰረት በማድረግ የሚተላለፍ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ለተጠሪ የተላከው መጥሪያ በስር ፍ/ቤት በ25/3/13 ዓ.ም እንዲላክ በታዘዘው መሰረት መጥሪያ ወጪ በሚሆንበት ጊዜ የችሎት ጸሃፊ በስህተት በ25/03/03 የተጻፈውን ተጠሪ በቀን 30/03/2013 ዓ.ም ፈርመው የወሰዱ ስለመሆኑ እንዲሁም መቼ መልስ ማቅረብ መቼ የቃል ክርክር እንደሆነ በግልጽ የሚያመለክት መሆኑን ሆኖም ተጠሪ በቀን/ዓ.ም አጻጻፍ ምክንያት በተገለጸው ቀነ ቀጠሮ ቀርበው መልስ አለማቅረባቸውን እና ፍርድ ቤቱ መልስ ማቅረብ መብታቸውን ማለፉን

የሚመለከት ነው፡፡ የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የቀን/ዓ.ም እና የተሰጠው ጊዜ አጭር መሆንን መሰረት በማድረግ መወሰኑን የሚመለከት ነው፡፡

ተከሳሽ የሆነ ወገን በሕጉ አግባብ የተላከለት መጥሪያ ደርሶት ለቀረበው ክስ የጽሑፍ መልስ ባያቀርብ ምን ውጤት እንደሚኖረው በተወሰነ መልኩ የተመለከተው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 233 ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ይዘት ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 199(1) ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲታይ ደግሞ መልሰ ለመቀበል የተያዘው የቀጠሮ ምክንያት ባይከበር ውጤቱ ሊሆን የሚችለው ተከሳሹ በጽሑፍ መልስ የማቅረብ መብት ማለፍ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 መሰረት ለቀጠሮው ምክያት የሆነው ነገር ባለመፈጸሙ ምክንያት ትእዛዝ ከሚሰጥባቸው ምክንያቶች ቀጠሮው ሳይከበር የቀረው በተከራካሪ ወገኖች ጉድለት የተነሳ ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ለቀጠሮ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው በተከራካሪዎቹ ወገኖች ጉድለት ያልሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሌላ ቀጠሮ መስጠት እንዳለበት በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (2) ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በቀጠሮው ዕለት ቀርቦ መልስ ያልሰጠበትን ምክንያት በመጥሪያው አጻጻፍ እና መልስ ለማዘጋጀት የነበረውን ጊዜ ፍርድ ቤቱ የተቀበለው በመሆኑ እነዚህ ምክንያቶች ደግሞ የተጠሪ ጉድለት አለመሆናቸው ተረጋግጠዋል፡፡

ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመጥሪያ አጻጻፍ ጉድለት እና ተጠሪ መልስ ለማቅረብ የነበረውን ጊዜ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤት የተጠቀሰውን ድንጋጌ መሰረት ሳያደርግ ተጠሪ መልስ በጽሁፍ የመስጠት መብቱ የታለፈው ያለአግባብ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ በተጠሪ ጉድለት ባልሆነ ምክንያት መልስ በጽሁፍ የመስጠት መብቱ የታለፈ መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በክ/መ/ቁ 90793 በግንቦት 19 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 271867 በግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በመሻሩ እና ይኸው በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 229564 በሰኔ 25 ቀን 2014 ዓ.ም በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>መዝገቡ ተዘግቷል</u>፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ